የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ ነሐሴ ፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 47
ADDIS ABABA 9th August, 2022

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፲፪፻፸፫/፳፻፲፬
የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን
አዋጅ....................................ገጽ ፲፫ሺ፬፻፩

## Content

Proclamation No.1273/2022
Community Based Health Insurance
Proclamation..............................page 4401

## አዋጅ ቁጥር ፲፪፻፸፫/፳፻፲፬

## የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አዋጅ

ዜጎች ለጤና አገልግሎት በሚያወጡት ከፍተኛ ወጪ ምክንያት ለከፋ ድህነት እየተዳረጉ ከመሆኑም በላይ አብዛኞቹ የሚከፍሉት ገንዘብ በማጣት ሊድኑ በሚችሉ ህመም እየተሰቃዩ ላልተፈለገ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ቀውስ እየተጋለጡ በመሆኑ፤

የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓትን በመዘርጋት በህብረተሰቡ መካከል ያለውን የእርስ በእርስ የመደጋገፍ ባህል በማጠናከር ፍትሐዊ፣ ጥራት እና ቀጣይነት ያለው ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ሽፋን ለዜጎች ተደራሽ በማድረግ ጤንነቱ የተጠበቀ አምራች ኃይል ማፍራት የሀገሪቱ የጤና ፖሊሲ አካል በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1273/2022

## COMMUNITY BASED HEALTH INSURANCE PROCLAMATION

**WHEREAS**, due to a significant rise in health service costs, citizens are forced to incur huge expenses that lead to impoverishment as well as leading many to suffer from preventable diseases;

**WHEREAS**, Community Based Health Insurance System solidifies the pre-existing custom of mutual support among the community and ensures access to equitable, quality, and sustainable health services to accelerate the move toward Universal Health Coverage; which in turn improves the productivity of citizens to enhance economic growth which is the primary goal of the country's health policy;

የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት በሙከራ ትግበራ ወቅት አበረታች ውጤት በማሳየቱ ቀጣይነቱን ይበልጥ ለማረጋገጥ በተበታተነ መልኩ ሲተገበር የቆየውን አሰራር ይበልጥ በተቀናጀ ሁኔታ የፌደራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላትን አስተሳስሮ ለመምራት የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ-አንቀጽ (፮) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አዋጅ ቁጥር ፲፪፻፸፫/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ "የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን" ማለት ትርፍን መሠረት ያላደረገ መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በአባልነት የሚያቅፍ የመድህን ዓይነት ነው፤

፪/ "መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተሰማሩ" ማለት በግብርና ሥራዎች፣ በአርብቶ አደርነት፣ በከፊል አርብቶ አደርነት፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተሰማርተው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩና በእነዚህ ተቋማት ተቀጥረው የሚሠሩ፣ የገቢ ምንጭ የሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን እንዲሁም በማህበራዊ የጤና መድህን አዋጅ ቁጥር ፮፻፺/፪ሺ፪ የማይሸፈኑትን ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች

**WHEREAS**, the encouraging results and lessons learned during the pilot phase of the Community Based Health Insurance System show a need for a national legal framework to ensure standardization for the sustainability of the system and allow better coordination at the Federal and Regional levels, thereby,

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Article (6) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

## PART ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Community Based Health Insurance Proclamation No.1273/2022".

**2. Definition**

In this Proclamation:

1/ **"Community Based Health Insurance"** means a non-profit health insurance arrangement that encompasses all sections of the society in the informal sector as members;

2/ **"Informal Sector"** means a sector that covers a section of the society whose livelihood depends on agricultural activities, pastoralism, semi-pastoralism, small and micro-enterprise operators and their employees, a section of the community with no income and unemployed and encompasses all anyone not covered under Social Health Insurance Proclamation No.690/2010;

፫/ "የኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፩/፪ሺ፲ የተቋቋመው እና የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ ስያሜው የኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት በሚል የተለወጠው ነው፡

3/ **"Ethiopian Health Insurance Service"** means the Ethiopian Health Insurance Agency established by Council of Ministers Regulation No.191/2010 and its name renamed to Ethiopian Health Insurance Service under Proclamation No.1263/2021 to determine the powers and functions of the executive organ;

፬/ "ቋት" ማለት በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት ውስጥ ከከፋይ አባላት መዋጮ ከተናጠል ድጎማ፣ ከአጠቃላይ ድጎማ እና ከሌሎች ምንጮች የሚገኘውን ገንዘብ በአንድ ላይ በማሰባሰብ ለተጠቃሚዎች የጤና አገልግሎት ለመግዛት የሚውል ሀብት ነው፡

4/ **"Pool"** means a fund made up of member contribution, targeted subsidy, general subsidy, and other sources used for procurement of health services for beneficiaries;

፭/ "አባል" ማለት ቤተሰቡን የሚያስተዳድር ባል ወይም ሚስት ወይም በሕግ የማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ሆኖ ራሱን እና ቤተሰቡን በጤና መድህኑ ያስመዘገበ እንዲሁም ራሱን ችሎ ዓመታዊ መዋጮ የከፈለ ወይም በሌላ ወገን የተከፈለለት ሰው ነው፤

5/ **"Member"** means a household head husband or wife or a person; registered for community-based health insurance and paid annual contribution or whose contribution has been paid by another;

፮/ "ቤተሰብ" ማለት መሠረታዊ እና ተጨማሪ የቤተሰብ አባላትን የሚያጠቃልል ነው፤

6/ **"Family"** shall include core and additional family members;

፯/ "መሠረታዊ የቤተሰብ አባል" ማለት የአባሉን የትዳር አጋርና ልጅን ይጨምራል፤

7/ **"Core Family"** means the spouse and children of a member;

፰/ "የትዳር አጋር" ማለት ከአባል ጋር በሕጋዊ ጋብቻ የተሳሰረ ሰው ሲሆን በቤተሰብ ሕጉ እንደባልና ሚስት የሚኖሩትንም ይጨምራል፤

8/ **"Spouse"** means a person legally married to a member and includes those in an Irregular Union as per the Family Law;

፱/ "ልጅ" ማለት እድሜው ከ፲፰ ዓመት በታች የሆነ የአባል ልጅ ወይም የጉዲፈቻ ልጅ ሲሆን አባሉ በሕግ መሠረት የአሳዳጊነት ኃላፊነት የተጣለበትን ማንኛውንም ልጅ የሚያጠቃልል ሆኖ ዕድሜያቸው ከ፲፰ ዓመት በላይ ቢሆንም ራሳቸውን ለማስተዳደር የማይችሉ የአዕምሮ ህመማንን ወይም የአካል ጉዳተኛ የሆኑ

9/ **"Child"** means the natural or adopted child of a member or any child under the guardianship of the member and has not attained majority, it includes a child over the age of 18 who is unable to sustain himself due to mental or physical disability;

፲/ "ተጨማሪ የቤተሰብ አባል" ማለት ከመሠረታዊ የቤተሰብ አባል ውጪ ሆኖ ከአባሉ ጋር በአንድ ጣሪያ ሥር የሚኖር እና በአባሉ ገቢ የሚተዳደርን ሰው ይጨምራል፤

፲፩/ "መክፈል የማይችል" ማለት በገቢ መጠን ልየታ መስፈርት መሠረት ዓመታዊ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን መዋጮ የመክፈል አቅም የሌለው ተብሎ በወረዳ አስተዳደር የተለየ አባወራ ወይም እማወራ ወይም ግለሰብ ነው፤

፲፪/ "የቅብብሎሽ ስርዓት" ማለት በህክምና ባለሙያ ትዕዛዝ መሰረት ታካሚዎች ከአንድ ጤና ተቋም ወደ ሌላ የጤና ተቋም የሚላኩበት የህሙማን አላላክ ስርዓት ነው፤

፲፫/ "የጤና አገልግሎት ተቋም" ማለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው የጤና አገልግሎት ለመስጠት በአስፈጻሚው አካል በሚወጣ መስፈርት ተመርጦ ውል የገባ የመንግስት ወይም የግል የጤና አገልግሎት ተቋም ነው፤

፲፬/ "የግል የጤና አገልግሎት ተቋም" ማለት በመንግስት የልማት ድርጅት፣ በበጎ አድራጎት፣ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ወይም በግል ባለሃብት የሚተዳደር ሆኖ ለትርፍ የተቋቋመ ወይም ለትርፍ ያልተቋቋመ የጤና አገልግሎት ተቋም ነው፤

፲፭/ "የጥቅም ማዕቀፍ" ማለት በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓቱ እንዲሸፈኑ የተለዩ የጤና አገልግሎቶች ናቸው፤

፲፮/ "ተጠቃሚ" ማለት የጥቅም ማዕቀፉን መጠቀም የሚችሉ አባል እና የአባሉን ቤተሰብ ያካትታል፤

10/ **"Additional Family Member"** means someone outside of the core family but lives under the same roof with the member and is dependent on the member's income;

11/ **"Indigent"** means household head or a person identified by the Woreda administration as being unable to afford annual membership contribution according to the income amount criteria;

12/ **"Referral System"** is a system in which a health professional transfers a patient from one health facility to another to provide additional treatment or services;

13/ **"Health Facility"** means any public or private health facility which has a competency certificate and is selected by the implementing body on the bases of criteria set out by it to enter into a contractual agreement to provide health services to beneficiaries;

14/ **"Private Health Facility"** means a health facility run by public enterprises, Charities, Non-Governmental Organizations, or private investors established for or not for profit;

15/ **"Benefit Package"** means health services covered by the community-based health insurance system;

16/ **"Beneficiary"** means a member and his family entitled to use the benefits package;

፲፯/ "የቀጥታ ክፍያ" ማለት ተጠቃሚው የጤና አገልግሎት በሚያገኝበት ወቅት በቁርጥ ወይም ከጠቅላላ የህክምና ወጪው ላይ በመቶኛ ተሰልቶ የሚከፍለው ክፍያ ነው፡

፲፰/ "የተናጠል ድጎማ" ማለት ከክልል መንግሥት ወይም ከወረዳ አስተዳደር ወይም በሁለቱም መክፈል ለማይችሉ የሚደረግ ዓመታዊ መዋጮ ነው፤

፲፱/ "አጠቃላይ ድጎማ" ማለት ከፌደራል መንግሥት በየዓመቱ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አባላት መዋጮ ለመደጎም የሚመደብ ገንዘብ ነው፤

፳/ "የስጋት ተጋላጭነት አስተዳደር" ማለት የጤና መድህን ሥርዓቱን የፋይናንስ ቀጣይነት አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ለመከላከል እና ለመቀነስ የሚወሰድ እርምጃ ነው፤

፳፩/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡

፳፪/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፫/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች እና በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ስርዓት ውስጥ በሚሳተፉ ተቋማት እና አስፈጻሚ አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

17/ **"Co-Payment"** means a lump sum or percentage of the total medical expense to be paid by the beneficiary;

18/ **"Targeted Subsidy"** means annual membership contribution allocated by regional government or Woreda administration or by both for the indigent household;

19/ **"General Subsidy"** means a subsidy allocated annually by the federal government to match the total membership contribution of the Community-Based Health Insurance System;

20/ **"Risk Management"** means a system and process employed to prevent and mitigate financial risks of the Community-Based Health Insurance System;

21/ **"Region"** means any state referred to in Article 47 of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

22/ **"Person"** means any natural or juridical person;

23/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall be applicable throughout the country to members of the informal sector, institutions, and executive bodies involved in the Community-Based Health Insurance System.

## ክፍል ሁለት
## የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት መቋቋም

**፬. መቋቋም**

የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**፭. የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ቋት ምሥረታ**

፩/ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ቋት በክልል እና በፌደራል ደረጃ ይመሠረታል፡፡

፪/ የክልል እና የፌደራል ቋት ድርሻ ከሚሰበሰበው አጠቃላይ መዋጮ በመቶኛ የተከፋፈለ ይሆናል፡፡

፫/ በክልል የሚቋቋመው ቋት እንደ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በክልል ወይም ከክልል በታች ባለ የአስተዳደር እርከን የሚመሠረት ሲሆን የክፍፍል ድርሻው በክልል ሕግ ይወሰናል፡፡

**፮/ የመጠባበቂያ ፈንድ**

፩/ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት የመጠባበቂያ ፈንድ በፌደራል እና በክልል አስተዳደር ደረጃ ይቋቋማል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቋቋመው የመጠባበቂያ ፈንድ ከተሰበሰበው አጠቃላይ ዓመታዊ የአባላት መዋጮ አምስት (፭) በመቶ ይሆናል፡፡

## PART TWO
## ESTABLISHMENT OF A COMMUNITY-BASED HEALTH INSURANCE SYSTEM

**4. Establishment**

This Proclamation hereby establishes the Community Based Health Insurance System.

**5. Establishment of Community-Based Health Insurance Pool**

1/ Community Based Health Insurance pool shall be established at the Regional and Federal levels.

2/ The Regional and Federal pool share shall be divided on a percentage basis from the total contribution.

3/ Regional pool may be established at the Regional or Sub-Regional level depending on the Region's context, and the pool's share shall be determined by Regional Law.

**6. Reserve Fund**

1/ Community Based Health Insurance shall have a Reserve Fund at the Federal and Regional levels.

2/ The total reserve fund amount shall be five (5) Percent of the total membership contribution, as stated under Sub-Article(1) of this Article

## ክፍል ሦስት

## የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አስፈጻሚ አካላት

**፯. የፌደራል አስፈጻሚ አካል**

፩/ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓትን የሚመራው፣ የሚያስተባብረው እና የሚያስፈጽመው የኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት ነው።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራል አስፈጻሚ አካል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

ሀ) የፖሊሲ ሃሳብ ያመነጫል፣ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ የሕግ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤

ለ) በሀገሪቱ ለሚመሰረቱ ቋቶች የአመሠራረት ሥርዓትና እና መለኪያ ያወጣል፤

ሐ) የፌደራል ቋቱን ያስተዳድራል፤ በሶስተኛ ደረጃ ሆስፒታሎች የጤና አገልግሎት ግዢ ይፈጽማል፤

መ) ለጤና መድህን ሥርዓቱ የሚውል አማራጭ የገንዘብ ምንጭ ያፈላልጋል፣ ሥርዓት ይዘረጋል፤

ሠ) ለክልል አስፈጻሚ አካላት የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፤

ረ) የሚያስፈልገውን ዓመታዊ አጠቃላይ ድጎማ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል አቅርቦ ያስመድባል፤

ሰ) የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት የዘላቂነት ተጋላጭነት መቀነሻ ስልት ይቀይሳል፣ እንዲተገበር ያደርጋል፤

## PART THREE

## COMMUNITY-BASED HEALTH INSURANCE IMPLEMENTING BODIES

**7. Federal Implementing Body**

1/ The Ethiopian Health Insurance Service shall lead, coordinate, and implement Community Based Health Insurance System.

2/ Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Federal Implementing Body shall have the following duties and responsibilities:

a) formulate policy recommendations, design strategies, and develop legal frameworks;

b) develop systems and set national standards to guide the establishment of pools;

c) administer the federal pool and procure health services from tertiary level health facilities;

d) design a mechanism to solicit alternative financial sources to strengthen the insurance system;

e) provide support to build the capacity of the regional implementing body;

f) ensure the allocation of annual general subsidy by the appropriate government body;

g) devise and execute the necessary risk mitigation mechanisms;

ሸ) የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓትን ለማዘመን አዳዲስ አሠራሮችና ቴክኖሎጂዎችን ይዘረጋል፣

ቀ) የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት አላማን ለማሳካት ሥራዎችን እንደአስፈላጊነቱ በሦስተኛ ወገን ሊያሰራ ይችላል፣

በ) የሥራ አፈጻጸሙን በተመለከተ ለሚቋቋመው ብሔራዊ ምክር ቤትና ለሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣

ተ) የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓትን ለማስፈጸም የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፫/ በደንብ ቁጥር ፩፻፺፩/፪ሺ፲ የተቋቋመው የሥራ አመራር ቦርድ በዚህ አዋጅ ለኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት የተሰጡ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥራዎችን በበላይነት ይመራል።

፰. <u>የክልል አስፈጻሚ አካል</u>

፩/ በክልል ደረጃ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓትን የሚያስፈጽም የክልል አስፈጻሚ አካል የሚቋቋም ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል የሚቋቋመው አካል እንደአግባብነቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

ሀ) በክልል የተለያየ የአስተዳደር እርከን የሚመሰረተውን ቋት ያስተዳድራል፣ በመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የጤና አገልግሎት ተቋማት የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ግዥ ይፈጽማል፣

h) introduce new practices and technologies to modernize the Community-Based Health Insurance System;

i) outsource specific duties as may be necessary to third parties for the proper implementation of Community-Based Health Insurance System functions;

j) submit a timely performance report to the National Community-Based Health Insurance Council and other relevant bodies;

k) perform other activities necessary to facilitate Community-Based Health Insurance functions.

3/ The Ethiopian Health Insurance Service management board established by Regulation No. 191/2010 shall oversee and supervise Community-Based Health Insurance Functions given under this Proclamation.

8. <u>Regional Implementing Body</u>

1/ Regions shall establish a regional implementing body to implement Community-Based Health Insurance System functions at the Regional level.

2/ Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Regional implementing body shall have the following duties and responsibilities:

a) administer pools to be established at different levels of administration in the region and procure health services from primary and secondary health facilities;

ለ) በክልል ደረጃ የሚቋቋመውን የመጠባበቂያ ፈንድ ያስተዳድራል፤

ሐ) በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ ተግባራትን ያከናውናል፤

መ) የቅስቀሳ ሥራን በመስራት የአባላት ምዝገባ ያከናውናል፤ መዋጮ ይሰበስባል፤ የአባልነት መታወቂያ በማዘጋጀት ያሰራጫል፤

ሠ) በመቶኛ ክፍፍሉ ልክ በየደረጃው የተፈጠረውን ቋት እና የመጠባበቂያ ፈንድ ድርሻ ያስተላልፋል ወይም መተላለፉን ያረጋግጣል፤

ረ) የተናጠል ድጎማ በጀት እንዲመደብ ክትትል ያደርጋል፤

ሰ) የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት አተገባበርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

ሸ) እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የተመሰረተው ዝቅተኛ ቋት ባለበት የአስተዳደር እርከን ላይ የሥራ አመራር ቦርድ እና ጠቅላላ ጉባኤ መመረጡን እና በአግባቡ እየሰራ መሆኑን ይቆጣጠራል፤

ቀ) የሥራ አፈጻጸሙን በተመለከተ ለክልል እና ለማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ብሔራዊ ምክር ቤት፣ ለፌደራል አስፈጻሚ አካል እና ለሌሎች አግባብነት አካላት ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፤

በ) በክልሉ ያለውን የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት አላማን ለማሳካት ሥራዎችን እንደአስፈላጊነቱ በሦስተኛ ወገን ሊያሰራ ይችላል፡፡

b) administer the reserve fund established at the Regional level;

c) undertake awareness creation activities on Community-Based Health Insurance;

d) mobilize and carry out member registration, collect membership contribution, issue and distribute membership identification cards;

e) transfer or ensure the transfer of pools' shares and reserve funds based on the determined percentage of allocation;

f) ensure timely allocation of targeted subsidy,

g) monitor and evaluate the implementation of the Community-Based Health Insurance System together with other stakeholders,

h) depending on the circumstances of the region, ensure the establishment and functionality of the executive board and general assembly at all primary level pools;

i) submit periodic performance reports to the Regional, and National Community Based Health Insurance Council, the Federal Implementing Body, and other relevant bodies;

j) outsource specific duties as may be necessary to third parties for the proper implementation of Community Based Health Insurance system functions of the region;

ተ.ደህን አዋጅ ተከትለው በሚወጡ ደንብ እና መመሪያዎች የተመለከቱትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፱. የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ምክር ቤት

፩/ የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ብሔራዊ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሰብሳቢነት የሚመራ የክልል የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ምክር ቤት ይቋቋማል፡፡ የአባላት ስብጥሩ፣ ተግባራት እና ዝርዝር አሠራሩ በክልሉ ህግ ይወሰናል፡፡

## ፲. የምክር ቤቱ አባላት

፩/ የምክር ቤቱ አባላት ሁሉም የክልል ርዕሳነ መስተዳድር፣ የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባዎች እንዲሁም አግባብነት ካላቸው አካላት የተውጣጡ ሆኖ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰየማሉ፡፡

፪/ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

፫/ የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር የምክር ቤቱ ጸሐፊ ይሆናል፡፡

## ፲፩. የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ ለማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት ትግበራ የሚረዱ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ይሰጣል፤

k) perform other duties in accordance with this Proclamation, Regulation and following Directives.

## 9. Community Based Health Insurance Council

1/ National Community Based Health Insurance Council (hereinafter the "Council") is hereby established.

2/ Regional governments wil also establish a regional Community-Based Health Insurance Council to be chaired by the regional state presidents. Members of the Council, Power of the Counciland detail work procedure shall be determined by Regional Law.

## 10. Membership in the Council

1/ Members of the Council shall be all regional state Presidents, mayors of Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations, and other members selected from relevant stakeholders and designated by the Deputy Prime Minister

2/ The Deputy Prime Minister shall be the chairperson of the Council.

3/ The Director-General of Ethiopian Health Insurance Service shall be the Secretary of the Council.

## 11. Powers and Duties of the Council

The Council shall have the following powers and duties:

1/ Give policy directions regarding the Community-Based Health Insurance System;

፪/ ዓመታዊ የአባልነት የመዋጮ መጠን፣ የቀጥታ ክፍያ መጠን፣ የጥቅም ማዕቀፍን እና የመድሀኒት ዝርዝር ይወስናል፤

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት የክልል እና የፌደራል ቋት ክፍፍል መቶኛ ይወስናል፤

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት በክልል እና በፌደራል ደረጃ የሚቀመጠውን የመጠባበቂያ ፈንድ ክፍፍል መቶኛ ይወስናል፤ ማሻሻያ ሲያደርግ ይችላል፤

፭/ ምክር ቤቱ በአዋጁ የተቀመጡ ዋና ዋና የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ተግባራትን አፈጻጸም አስመልክቶ በኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት የሚቀርበውን የክንውን ሪፖርት ይገመግማል፤ የማሻሻያ ሃሳቦችን ይሰጣል፤

፮/ ይህ አዋጅ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ መሆኑን ይገመግማል፤ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች እንዲፈቱ ለሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን መመሪያ ይሰጣል፤

፯/ ለሥርዓቱ ውጤታማነት የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሠራር እና ተሳትፎ ቀጣይነት እንዲኖረው አቅጣጫ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

## ፲፪. የምክር ቤቱ ስብሰባ

፩/ ምክር ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ የተገኙበት ስብሰባ ላይ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

2/ Set the annual membership contribution, co-payment, benefit package, and decice on the list of medicine;

3/ Decide the percentage share of regional and federa. pool pursuant to Article 5 Sub- Article (2) of this Proclamation;

4/ Determine the share of regional and federal reserve funds; amend the percentage share as may be necessary, pursuant to Article 6 Sub-Article (2) of this Proclamation;

5/ Review the performance report of the Ethiopian Health Insurance Service on the implementation of the significant Community Based Health Insurance activities set out in the Proclamation; provide suggestions for improvement;

6/ Review the nationwide implementation of this Proclamation and give directions to relevant stakeholders seek solution to challenges;

7/ Create a platform for integration of stakeholders to ensure the proper performance of health insurance functions, follow up its implementation;

## 12. Meetings of the Council

1/ The Council shall meet twice a year, provided it may hold an extraordinary meeting whenever necessary.

2/ The presence of more than half of the members of the Council shall constitute a quorum.

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ይሆናል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት እና አሠራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## ስለ አባልነት፣ መዋጮ እና የጥቅም ማዕቀፍ

### ፲፫. አባልነት

፩/ መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ የተሰማራ ማንኛውም ሰው የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አባል ይሆናል።

፪/ አባልነት በቤተሰብ ደረጃ ሆኖ ምዝገባው በአባወራ ወይም በእማወራ ይከናወናል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ቢኖርም አባልነት በግለሰብ ደረጃ ሊሆን ይችላል፡፡

### ፲፬. የምዝገባ እና የእድሳት ጊዜ

፩/ የአባልነት ምዝገባ ለአንድ ዓመት የፀና ሆኖ በየዓመቱ መታደስ ይኖርበታል።

፪/ የአባልነት ምዝገባ እና እድሳት በዓመት አንድ ጊዜ ሆኖ ለተከታታይ ሁለት ወራት ብቻ የሚከናወን ይሆናል።

፫/ አግባብ ያለው የክልል አስፈጻሚ አካል የምዝገባ እና የእድሳት ጊዜ የአካባቢውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ ሊወስን ይችላል።

### ፲፭. የአባልነት መዋጮ

፩/ አባላት በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ስሥርዓቱ ዓመታዊ መዋጮ ይከፍላሉ።

3/ The Council shall pass decisions through majority votes, and the charperson shall have a casting vote in case of a tie.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its rules of procedures.

## PART FOUR
## MEMBERSHIP, CONTRIBUTION, AND BENEFIT PACKAGE

### 13. Membership

1/ Every member of the informal sector shall be a member of the Community Based Health Insurance.

2/ Memberships shall be at the family level, and the household head shall make the registration of the household.

3/ Notwithstanding Sub-Article (2), of this Article membership may be at an individual level.

### 14. Registration and Renewal Period

1/ Registration will be valid for one year and must be renewed annually.

2/ Member registration or renewal will be carried out once a year for two consecutive months only.

3/ The respective regional implementing body shall determine the registration and renewal period.

### 15. Membership Contribution

1/ Members shall pay annual contributions to the Community Based Health Insurance System.

፪/ ለመሠረታዊ የቤተሰብ አባላት የሚከፈለው የመዋጮ እንደተጠበቀ ሆኖ ለተጨማሪ የቤተሰብ አባላት ተጨማሪ ክፍያ የሚከፈል ይሆናል።

፫/ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት ዓመታዊ መዋጮ የሚሸፈነው በአባሉ እና በመንግሥት አጠቃላይ ድጎማ ይሆናል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) መሠረት የሚደረገው የአጠቃላይ ድጎማ መጠን የመዋጮ መጠኑ ፳፭ በመቶ ይሆናል።

፭/ መክፈል ለማይችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ዓመታዊ የአባልነት መዋጮ በተናጠል ድጎማ ይሸፈናል።

፮/ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን የመዋጮ መጠን የጤና አገልግሎት ወጪ እና የህብረተሰቡን የመክፈል አቅም ባገናዘበ ሁኔታ በከተማ እና በገጠር እንዲሁም በገቢ እርከን የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡

**የጥቅም ማዕቀፍ**

፩/ ለማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ተጠቃሚዎች የሚሸፈነው የጤና አገልግሎት የጥቅም ማዕቀፍ በሀገሪቱ መሠረታዊ የጤና አገልግሎቶች ዝርዝር ከተካተቱት ውስጥ ይሆናል፡፡

፪/ የተፈቀደው የጤና አገልግሎት የጥቅም ማዕቀፍ ለተጠቃሚዎች የሚሰጠው ከፌደራል ወይም ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር ውል ከገቡ የጤና አገልግሎት ተቋማት ይሆናል፡፡

2/ A contribution will be paid for core family members, and an additional fee shall be paid for additional family members.

3/ The annual contribution to the Community Based Health Insurance System shall be covered by the member and the Government in the form of a General Subsidy.

4/ The amount of the General Subsidy to be made pursuant to Sub-Article (3) of this Article shall be 25 Percent of the total annual contribution.

5/ The annual contribution of indigents shall be covered through targeted subsidy.

6/ Community Based Health Insurance contribution amount may vary with income level and between urban and rural settings by considering the community's ability to pay and the cost of health services.

**16. Benefit Package**

1/ The benefit package for the beneficiaries will be from the essential health service package.

2/ The benefit package covered by the Community Based Health Insurance System shall be provided to beneficiaries through health facilities entering a contract with Federal or Regional implementing bodies.

# ክፍል አምስት

## የፋይናንስ ምንጮች እና አስተዳደር

**፲፯. የፋይናንስ ምንጮች**

የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን የፋይናንስ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ ከከፋይ አባላት የመመዝገቢያ ክፍያ እና የአባልነት መዋጮ፣

፪/ ከተናጠል ድጎማ፣

፫/ ከአጠቃላይ ድጎማ፣

፬/ ከልማት አጋሮች፣ ከግለሰቦች ወይም ከተቋማት የገንዘብ ድጋፍ፣

፭/ ሌሎች ምንጮች፡፡

**፲፰. የፋይናንስ አጠቃቀም**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ከተዘረዘሩት የገቢ ምንጮች የሚሰበሰበው ገቢ ለተጠቃሚዎች የጤና አገልግሎት ወጪ የሚውል ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚሰበሰበው ገቢ ለሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጥቃቅን ወጪዎች ሊውል ይችላል፡፡ መጠኑ በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ብሔራዊ ምክር ቤት የሚወሰን ሆኖ ዝርዝር አፈጻጸሙ የኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

**፲፱. የፋይናንስ አስተዳደር እና ቁጥጥር**

፩/ በየደረጃው ያሉ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አስፈጻሚ አካላት የተሟላ እና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛሉ።

# PART FIVE

## SOURCE OF FINANCE AND ADMINISTRATION

**17. Source of Finance**

Sources of finance for the Community Based Health Insurance are:

1/ Registration fee and membership contribution;

2/ Targeted subsidy;

3/ General subsidy;

4/ Financial support from development partners, individuals, and organizations;

5/ Other sources.

**18. Finance Utilization**

1/ The resource acquired according to Article (17) of this Proclamation shall be used to pay for the health service of beneficiaries.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the resources collected may also be used for other petty expenditures. Amount shall be determined by a National Community Based Health Insurance Council, and the detailed implementation shall be determined by a Directive of the Ethiopian Community Based Health Insurance Service.

**19. Finance Administration and Control**

1/ The Regional and Federal Administrative Bodies shall keep complete and accurate financial records at all levels.

፪/ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን የፋይናንስ አጠቃቀምና አስተዳደር ሥርዓት አግባብነት ባለው የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ሕግ ይመራል፣ ኦዲት ይደረጋል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ይቀርባል፡፡

፳. <u>የፋይናንስ ጉድለት አሸፋፈን</u>

፩/ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት የፋይናንስ ጉድለት በሚያጋጥመው ጊዜ ጉድለቱ ከመጠባበቂያ ፈንድ ይሸፈናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል ደረጃ ያጋጠመው የፋይናንስ ጉድለት በክልሉ ከተቀመጠው የመጠባበቂያ ፈንድ በላይ ሲሆን ቋቱ የተመሰረተበት የአስተዳደር እርከን ጉድለቱን የሚሸፍን ይሆናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራል ቋቱ ያጋጠመው የፋይናንስ ጉድለት በፌደራል ደረጃ ከተቀመጠው የመጠባበቂያ ፈንድ በላይ ሲሆን ጉድለቱን የፌደራል መንግሥት ይሸፍናል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>የስጋት ተጋላጭነት አስተዳደር</u>

፳፩. <u>የቅብብሎሽ ሥርዓት</u>

፩/ ማንኛውም ተጠቃሚ የጤና አገልግሎት ማግኘት የሚችለው የተዘረጋውን የቅብብሎሽ ሥርዓት በመከተል ይሆናል፡፡

፪/ የቅብብሎሽ ሥርአቱን ያልተከተለ ማንኛውም ተጠቃሚ የጤና አገልግሎት ወጪ በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አይሸፈንም፡፡

2/ The financial administration and utilization of the Community-Based Health Insurance shall be governed and audited according to the relevant government financial administration laws and reported to relevant bodies.

**20. <u>Deficit Coverage</u>**

1/ When a Community-Based Health Insurance System faces financial deficits, the reserve fund shall cover the deficit.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, when the Regional financial deficit is beyond the amount set aside in the Regional reserve fund, the deficit shall be covered by the administrative level where the pool is established.

3/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Federal Government shall cover the shortfall when the federal pool faces a financial deficit beyond the amount set in the federal reserve fund.

## <u>PART SIX</u>
## <u>RISK MANAGEMENT</u>

**21. <u>Referral System</u>**

1/ Beneficiaries can access health services only by following the established referral system.

2/ Cost of health services for any beneficiary who bypasses the referral system shall not be covered by Community-Based Health Insurance.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ለድንገተኛ ሕክምና ተጠቃሚው የቅብብሎሽ ሥርዓቱን ለመከተል አይገደድም፡፡

**፳፪. <u>የክፍያ እና የህክምና አገልግሎት ኦዲት</u>**

አግባብነት ያለው የፌደራል ወይም የክልል አስፈጻሚ አካል ከጤና አገልግሎት ተቋማት በቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ የክፍያ እና የህክምና አገልግሎት ኦዲት ያከናውናል፣ ክፍያም ይፈጽማል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፫. <u>የጤና አገልግሎት ተቋም ግዴታ</u>**

የጤና አገልግሎት ተቋም፡-

፩/ የሚሰጠው የጤና አገልግሎት አግባብ ያለው አካል ያወጣውን ብሔራዊ የጤና ክብካቤ ደረጃ የማሟላት፤

፪/ ለተጠቃሚው የሚሰጠው የጤና ምርመራ ወይም ህክምና በወጣው ስታንዳርድ የህክምና ጋይድላይን መሠረት መሆኑን የማረጋገጥ፤

፫/ የፌደራል ወይም የክልል አስፈጻሚው አካል በሚያከናውናቸው የህክምና አገልግሎት ኦዲት እና ተመሳሳይ ሥራዎች ትብብር የመተባበርና መረጃ የመስጠት

ግዴታ አለበት፡፡

**፳፬. <u>የአባል ግዴታ</u>**

አንድ አባል፡-

፩/ የእርሱንና የቤተሰቡን ትክክለኛ መረጃ የመስጠት እና የማስመዝገብ፤

3/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, it is not mandatory to follow the referral system for medical emergency cases.

**22. <u>Payment and Medical Audits</u>**

The appropriate Federal or Regional implementing body shall conduct a medical and claim audit on the payment request submitted by the health facilities and make the necessary payments. The detailed implementation shall be determined by a Directive of Ethiopian Health Insurance Service.

## PART SEVEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**23. <u>Responsibilities of Health Facility</u>**

Health facilities:

1/ Shall ensure health services provision meets the national health care standards set by the relevant body;

2/ Shall ensure the health service provided to beneficiaries is in accordance with the standard treatment guidelines;

3/ Shall cooperate and provide any information during medical and claim audits conducted by the Federal or Regional implementing body.

**24. <u>Responsibilities of the Member</u>**

A member:

1/ Shall get family members enrolled and provide accurate information about them;

፪/ የተሰጠውን የአባልነት የመታወቂያ ካርድ በጥንቃቄ የመያዝ፣ ለተፈቀደለት የቤተሰብ አባላት ብቻ እንዲጠቀም የማድረግ እና ለሌላ ወገን አሳልፎ ያለመስጠት፤

፫/ የምዝገባ እና የአባልነት ክፍያ የመክፈል፤ እና

፬/ በውልደት እና በጉዲፈቻ የተጨመሩ፣ ለአካለ መጠን የደረሱ ወይም በሞት የተለዩ የቤተሰብ አባላትን በወቅቱ የማሳወቅ

ግዴታ አለበት።

## ፳፭. የተጠቃሚ ግዴታ

ማንኛውም ተጠቃሚ፦

፩/ ለሕክምና ሲሄድ የአባልነት መታወቂያ ካርድ መያዝና ሲጠየቅም የማሳየት፣

፪/ የተሰጠውን የአባልነት የመታወቂያ ካርድ በጥንቃቄ የመያዝ እና ለሌላ ወገን አሳልፎ ያለመስጠት

ግዴታ አለበት።

## ፳፮. መረጃን በሚስጥር ስለ መጠበቅ

፩/ ማንኛውም የፌደራል ወይም የክልል አስፈጻሚ አካል ሠራተኛ ተጠቃሚን የሚመለከት የግል ወይም የሕክምና መረጃ በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

፪/ የግል ወይም የሕክምና መረጃን በሚስጥር ስለመጠበቅ በሚመለከት የወጡ ሌሎች ሕጎች በፌደራል ወይም በክልል አስፈጻሚው አካል ሠራተኞ እና ከአስፈጻሚው አካል ጋር የአገልግሎት ስምምነት ባላቸው አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ፳፯. አስተዳደራዊ እርምጃ

፩/ በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት ውስጥ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጡ ሕጎችን ጥሶ ከተገኘ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል።

2/ Shall keep the membership identification card with due care, not passing it over to an unauthorized third party;

3/ Shall pay registration and membership fees; and

4/ Duly disclose the change in vital family information such as birth, adoption, death, and attainment of majority.

## 25. Responsibilities of a Beneficiary

Any beneficiary:

1/ Shall provide membership identification card when visiting health facilities;

2/ Shall keep membership identification card with due care and shall not pass it over to an unauthorized third party.

## 26. Confidentiality of Information

1/ Every employee of the Federal or Regional implementing body shall keep the secrecy of member's personal or medical information.

2/ Other laws relating to the confidentiality of personal or medical information shall apply to Federal or Regional implementing body employees and entities with service agreements with the implementing body.

## 27. Administrative Action

1) Any person participating in a Community Based Health Insurance System shall be subject to administrative action if found to violate this Proclamation or the subsequent laws.

፪/ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ይህንን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ሕጎችን መተላለፉ ሲታወቅ አግባብ ባለው የጤና ባለሙያዎች ተቆጣጣሪ አካል በማጣወቅ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድበት ይደረጋል።

2/ If any health professional has violated this Proclamation or the subsequent laws, the appropriate action shall be taken by the relevant body governing health professionals.

## ፳፰. የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት

፩/ ቅሬታዎችን የሚቀበል እና ውሳኔ የሚሰጥ አካል በፌዴራል እና በክልል አስፈጻሚ ደረጃ ይደራጃል፡፡ ዝርዝር አደረጃጀት እና አሠራር ሥርዓቱ እንደአግባብነቱ በፌደራል ወይም በክልል አስፈጻሚው አካል በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ በቅሬታ ሰሚ አካል በሚሰጥ ውሳኔ ያልረካ ቅሬታ አቅራቢ በፌደራል ደረጃ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ በአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ለከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤት እንዲሁም በሌሎች ክልሎች ለወረዳው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል።

## 28. Complaints Handling

1/ The Federal and Regional implementing bodies shall establish a complaint handling body. Details of the structure and working procedure shall be determined by the Directive of the respective Federal or Regional implementing body.

2/ In cases where the complainant is not satisfied by the final decision of the complaint handling body, may appeal to the Federal First Instance Court at the Federal level, the Addis Ababa and Dire Dawa City Administration to the city Affairs Court, and to the Woreda Court in other Regions.

## ፳፱. ቅጣት

በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ተከትለው በሚወጡ ሌሎች ሕጎች ላይ የተቀመጡትን ክልከላዎች በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ሰው አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 29. Penalty

Any person who violates the provisions of this Proclamation or other subsequent laws shall be punished according to the appropriate law.

## ፴. የመተባበር ግዴታ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የተቀመጡ ኃላፊነት እና ግዴታዎችን ለመወጣት የሚመለከታቸው የፌደራል እና የክልል መንግሥት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 30. Obligation to Cooperate

Relevant Federal and Regional bodies shall have the obligation to cooperate with the implementing body to fulfill its duties and obligations outlined in this Proclamation.

**፴፩. <u>ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ የኢትዮጲያ ጤና መድህን አገልግሎት ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

**፴፪. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**፴፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**31. <u>Power to Issue a Regulation and Directive</u>**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ Ethiopian Health Insurance Service may issue Directives for the implementation of this Proclamation and Regulations issued according to Sub-Article (1) of this Article.

**32. <u>Non-Applicable Laws</u>**

Any law or customary practice inconsistent with this Proclamation shall have no effect on matters coverd by this Proclamation.

**33. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force from the publication date in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 9th Day of August, 2022**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**